የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

ታህሳስ 21/2001

# በበዓሉ ሰሞን የመብት ረገጣ ሰለባ የሆኑ ወገኖችን ሁሉ እናስታውሳቸው

በየምስጢር እስር ቤቶች፣ በትግራይ የጉድጓድ ማጎሪያዎች፣ በዴዴሳ፣ብር ሸለቆ፣ ዝዋይ፣ ብር ሸለቆ፣ በቃሊቲና ልዩ ልዩ እስር ቤቶች መብታቸው ተገፎ የሚሰቃዩትን ብዙ ሺ ዜጎች ልናስታውሳቸው፣ ሰቆቃቸው ሊሰማንና በደላቸው ሊቆጠቁጠን ይገባል፡፡ በተለይ የተረሱትን እስረኞች መከራ አስበነው “ ይፈቱ በአስቸኳይ!” ጩኸታችንን ማስማት የዜግነት ግዴታችን ሆኖ ይገኛል፡፡

ብርቱካን ኪድቂሳ ተያዘች፣ ቴዲ አፍሮ ተፈረደበትና ቃሊቲ ገባ -- ለምን ህግ ተጣሰ፣ለምን ህገወጥ እገታ ተካሄደ ብለን መቆጣትና ይፈቱ ማለት ተገቢ ነው፡፡ ታምራት ላይኔ የታሰረው በፖለቲካ በቀል ምክንያት ነውና ሲፈታ ምንም እንኳን በስልጣን ሳለ ለሕዝብ መብት መረገጥ አንዱ ተጠያቂ የነበር ቢሆንም መልካም ማለቱ ተገቢ ነው፡፡ ታምራት ሲለቀቅ አበራ የማነ አብስ? ሌሎች በገፍ ታስረው እየታሰቃዩ ያሉትስ? በዓለም ያሉ የሰብዓዊ መብት ተከላካይ ተቋሞች ነን የሚሉትና ኢሠመጉ ራሱስ ቢሆን ለምን ሌሎች እስረኞችን የት ደረሱ አይሉም? ለምን በየማጎሪያው የተጣሉትንና ለበሽታና ዱላ ተጋልጠው ያሉትን እስረኞች አናነሳቸውም? ፀጋዬ ገብረ መድህን፣ ይስሐቅ ደብረፅዮን፣ ስጦታው ሁሴን፣ አምሀ በለጠ ፣ ሀጎስ በዛብህ፣ አበራሽ በርታ፣ ለማ ኃይሌ፣ ተስፋዬ ከበደ ፣ ሞት ባይኖር፣ አበበ አይነ ኩሉ ፣ ተክላይ ገብረ ስላሴ፣ አዛናው ደምሌ፣ ታምራት ግዛቸው፣ ድንቁ ሺፈራው፣ ሻለቃ አዱኛ አደመ ፣ወንዱ ሲራክ ደስታ፣ ብርሃኑ እጅጉ፣ ደሳለኝ አምሳሉ፣የኦጋዴን፣የጋምቤላ ተወላጆች፣ እነ ተስፋዬ፣ደምሴና ሌሎች ከጋሞ ጎፋ፣ አያሌ የጦር መኮንኖች፣ በርካታ የራሱ የወያኔ ድርጅት አባላት ታፍነው ሲሰቃዩ ዓመታት አልፈዋል፡፡ ብዙዎቹ የት እንደደረሱም አይታወቅም፡፡ የት አደረሳችኋቸው? ደብዛቸው ለምን ጠፋ? ስለተወሰኑ እስረኞች ብቻ ለምን ጩኸቱ በርክቶ ሌሎች ይረሳሉ ብለን መጠየቅና መቃወም ይጠበቅብናል፡፡

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ የተመሰረተው የተረሱ የፖለቲካ እስረኞች ላይ በማተኮር ድምፅ አልባ ለሆኑት አንደበት ለመሆን ነው፡፡ ሳለፉት 13 ዓመታትም ይህን ሲራ ቆይቷል፡፡ ዛሬ የመብት ረገጣው ተባበሰ እንጂ አልቀነሰም፡፡ በ1997 ከተያዙት የታወቁት ሲለቀቁ ሺዎች ዛሬም እንደታፈኑ ናቸው፡፡ የኢሕአፓ አባላት የሆኑ እስረኞች ጉዳይ በብዙዎች አይነሳም፡፡ አበራ የማነአብን የሚያነሱ ብዙ አይደሉም፡፡ ሰብዓዊ መብት ለእነገሌ ሌሎች ግን የራሳቸው ጉዳይ የሚሉ ራሳቸውን

የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ከሚሉ ተቋሞች ጋር የኢፖእአ ኮሚቴ መሰረታዊ ልዩነት አለው፡፡ ለሕዝብ መብት በመቆማቸው ለእስር የተዳረጉና ደብዛቸው የጠፋ እስረኞች ሁሉ የምንጮህላቸው ናቸው፡፡ በመገናኛ ብዙሀን ትኩረት ለተሰጣቸው ብቻ ሳይሆን በተለይም ላልተሰጣቸው ጠበቃና አንደበት እንሁን፡፡ ገና አዲስ 2009 ዓመት ብለን የምናከብር ሁሉ እስቲ በዓል ለማክበር ያልበቁትና የታሰሩ ወገኖቻችን እናስባቸው፡፡

ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!!
የኢፖእአኮን ጥረት እንደግፍ!!


INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE